የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፬ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 47
ADDIS ABABA 1ST February 2008

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፶፫//፪ሺ.
የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ..............................................፬ሺ.፩፻፵፪

## CONTENTS

Regulation No. 153/2008
Customs Tariffs (Amendment) Council of Ministers Regulation Page............4142

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፫/፪ሺ.

### የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ::

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፫/፪ሺ." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

ከጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) ጋር ተያይዞ የሚገኘው የጉምሩክ የዕቃ ቀረጥ ሥርዓ ትና ተመን ሠንጠረዥ እንደገና ተሻሽሏል፡

### Council of Ministers Regulation No.153/2008

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND CUSTOMS TARIFFS REGULATION

This Regulation is issued by the Councl of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 4 of the International Convention on the Harmonized Descriptions and Coding System Ratification Proclamation No. 67/1993.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Customs Tariffs (Amendment) Council of Ministers Regulation No. 153/2008".

2. *Amendment*

   The Customs Tariffs Classification System of Goods and Rates Schedule attached to the Customs Tariffs Council of Ministers Regulation No. 122/1993 (as amended) is hereby further amended by the Schedule attached to this Regulation.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
P.O.Box 8001

፫. የሚኒስቴሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣

፩. የሸቀጦች አሰያየምና ምደባ የተሳሳተ ሆኖ ሲያገኘው ስህተቱ እንዲስተካከል ለማድረግ፣

፪. በዓለም ዓቀፍ የተዋሀደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓት ኮንቬንሽን መሠረት የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ክለሳ ሲደረግ ይህንኑ ተከትሎ የአሰያየምና አመዳደብ ማስተካከያ ለማድረግ፣ እና

፫. ከታሪፍ ከለላ ጋር በተያያዘ ምክንያት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴሮችና ሌሎች አካላት ጋር በመመካከር የገቢና ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ለመወሰን ወይም ለማሻሻል፣

የሥልጣን ውክልና በዚህ ደንብ ተሰጥቶታል፡፡

፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፪ሺ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፪ሺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Power of the Ministry*

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby given a power of delegation:

1) to correct any misclassification of goods;
2) to adopt revised versions of classification of goods pursuant to the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding System; and
3) where it is found necessary for purposes of tariff protection and upon consultations with the relevant ministries and other organs, to determine or amend customs tariffs.

4) *Effective Date*

This Regulation shall enter into force on the 1st day of January 2008.

Done at Addis Ababa, this 28 this day of December 2007

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት